**NOTE**

# National Benefits of Ethiopia's Digital ID Project and Its Implementation

Belayhun Yirga ♣

## Abstract

Identification system is divided into Foundation ID and Functional ID. There is the need for foundational ID in Ethiopia that fulfills international standards even though Kebele ID serves as a *de-facto* foundational ID. Driving license, work ID, bank passbook and other IDs are considered as functional ID. The Kebele ID is not backed by technology. It does not uniquely identify a person and is open for fraud. The Government of Ethiopia is thus implementing foundational digital ID by using modern technology. Ethiopia's digital ID is expected to strengthen national peace and security, national development planning, good governance and avert duplication of efforts, and eliminate the risk of exclusion in development works. The Ethiopian Digital ID Proclamation No. 1284/2023 is meant to enable the smooth implementation of digital ID in Ethiopia and has drawn lessons from the comparative experience of other countries. Registration for digital ID has three modalities. The *first* modality is through the registration centers of the institution; *secondly* through registration of clients by partner organizations; and the *third* modality of registration is conducted (with modest service charges) by entities permitted by the institution. The first and the second registration modalities are currently being implemented. The third modality requires establishing a policy direction and operating procedures, and it may not be implemented soon. The implementation of the first and the second modalities are expected to ensure effective registration within a short period of time. The digital ID registration process is expected to be completed within three to five years. As the Proclamation pursues the minimal data paradigm, the demographic data required for a digital ID are first name, father's name, grandfather's name, citizenship, date of birth (including month and year), gender and domicile address. Moreover, mother's name, telephone number, as well as email and postal address can be included. The biometric data collected for obtaining a digital ID are limited to ten fingerprints, iris of both eyes, and facial photo.

## Key terms

Fayda Identification Number · Digital ID · Foundational ID · Functional ID

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v17i2.8

**Suggested citation**:

Belayhun Yirga (2023). "National Benefits of Ethiopia's Digital ID Project and Its Implementation" (Amharic), 17(2) *Mizan Law Review*: 457-478.

♣ Belayhun Yirga (LLB, LLM), National ID Program, Senior Policy and Legal Advisor
Email: belayhunyirga2@gmail.com
ORCID: https://orcid.org/0009-0003-0352-5785

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት ሀገራዊ ፋይዳ እና አተገባበሩ

በላይሁን ይርጋ*

## አፅህሮተ ጽሑፍ

*የመታወቂያ ሥርዓት መሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት እና አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ መሥፈርቱን የሚያሟላ መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት ባይኖርም፣ የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት እንደመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት እያገለገለ ነው፡፡ መንጃ ፈቃድ፣ የመሥሪያ ቤት መታወቂያ፣ የባንክ ሂሳብ ደብተር እና የመሳሰሉት ደግሞ አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ዓይነቶች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ያለው መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት ወይም በሌላ አባባል የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ከሌሎች ሀገሮች መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት የሚለየው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ፣ እጅግ ኋላ ቀር፣ አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ መታወቂዎችን እንዲያወጣ ዕድል የሚሰጥ እና የመታወቂያውን ባለቤት በልዩ ሁኔታ ለመለየት የማያስችል መሆኑ ነው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በኢትዮጵያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገ፣ ከአገልግሎት ዘርፍ የመታወቂያ ሰነድነት ባሻገር ማንነትን የሚያረጋግጥ መሠረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለመዘርጋት ትግበራ ተጀምሯል፡፡ ሀገራዊ ሰላምና ደህንነትን ለማጠናከር፣ ሀገራዊ ልማትን በአግባቡ ለማቀድ፤ ምጣኔ ሀብታዊ ሽግግር ለመፍጠር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና ፖሊሲዎች ሲቀረጹ እና ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን እና አካታች ያለመሆን ችግርን በመቅረፍ ረገድ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ የኢትዮጵያን የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውጤታማ ለማድረግ አዋጅ ቁጥር 1284/2014 ወጥቶ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ አዋጁ ከሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ የተሻሉ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባን ተግባራዊ ለማድረግ የታሰበው በሦስት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው መንገድ የዲጂታል መታወቂያ ተቋሙ በራሱ እንዲመዘግብ ማድረግ፣ ሁለተኛው የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን የሚጠቀሙ አካላት ደንበኞቻቸውን ራሳቸው እንዲመዘግቡ ማድረግ፣ እና ሦስተኛው መንገድ ከተቋሙ ፈቃድ ወስደው ከተመዝጋቢዎች ላይ አነስተኛ ክፍያ እያስከፈሉ የሚመዘግቡበት ሥርዓት ነው፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ ሂደቱ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ይፈጃል ተብሎ ይገመታል፡፡ አዋጁ የተመጠነ የመረጃ ሥርዓት የሚከተል በመሆኑ፣ ለምዝገባ ተፈላጊ የሆኑት የዲሞግራፊክ መረጃዎች ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም፣ ዜግነት፣ የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመት፣ ፆታ እና መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ ናቸው፤ ከዚህ በተጨማሪ የእናት ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም ኢሜይልና የፖስታ አድራሻ ሊካካቱ እንደሚችሉ አዋጁ ይደነግጋል፡፡የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የሚሰበሰቡ የባዮሜትሪክ መረጃዎችም የተመጠኑና አሥር የጣት አሻራዎች፣ የፊት ገፅታ ፎቶና የሁለት ዓይን ብሌን ብቻ የሚካተቱበት ነው፡፡*

**ቁልፍ ቃላት**

ፋይዳ ቁጥር፣ ምዝገባ፣ ዲጂታል መታወቂያ፣ መሠረታዊ መታወቂያ፣ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ

**የጥቅስ አጠቃቀም**

በላይሁን ይርጋ (2016 ዓ.ም.)፣ "የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት አገራዊ ፋይዳና አተገባበሩ"፣ *ሚዛን የሕግ መጽሔት*፣ ቅጽ 17፣ ቁ. 2፣ ገጽ 431-452

* በላይሁን ይርጋ (ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም)፣ በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ የፖሊሲና ሕግ አማካሪ

ኢሜይል: belayhunyirga2@gmail.com

ORCID: https://orcid.org/0009-0003-0352-5785

## ይዘት

1. መግቢያ
2. የመታወቂያ ሥርዓቶች
   2.1. መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት
   2.2. አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት
3. በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የመታወቂያ ሥርዓት
   3.1. መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት
   3.2. አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት
4. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ሀገራዊ ፋይዳ
   4.1. በኢኮኖሚ ዘርፍ
   4.2. በማኅበራዊ ዘርፍ
   4.3. በፖለቲካ ዘርፍ
5. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት የሕግ ማዕቀፍና አተገባበር
   5.1. የሕጉ ዓላማ
   5.2. የሕጉ የተመጠነ መረጃ ሥርዓት ባህርይ
   5.3. በሕጉ አተገባበር ረገድ የመረጃ አጠባበቅ ሥርዓት
6. በዲጂታል መታወቂያ ትግበራ ሂደት የምዝገባ ሥርዓት
7. ማጠቃለያ

## 1. መግቢያ

ዓለም ባንክ እ.አ.አ. በ2017 ባደረገው ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ1.1 ቢሊዮን በላይ የሆኑ ሰዎች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምንም ዓይነት ሰነድ የሌላቸው መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን፣ ይህ ቁጥር እ.አ.አ. በ2021 ወደ 850 ሚሊዮን ዝቅ ማለቱን ይፋ አድርጓል፡፡[1] ከዚህ ቁጥር ውስጥ 81% የሚሆኑት የሚኖሩት ከሰሀራ በታች ባለው የአፍሪካ ክፍል እና በደቡብ እስያ ውስጥ ነው፤ ከእነዚህ መካከል 47% የሚሆኑት ሕፃናት ናቸው፡፡ ከላይ ከተገለፀው ቁጥር ውስጥ ከ63% በላይ የሚሆኑት ዝቅተኛ-መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ውስጥ የሚገኙ ናቸው፤ 28% የሚሆኑ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት[2] ውስጥ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ 850 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያገለግል ሰነድ የሌላቸው በመሆኑ ከመንግሥት እና ከግሉ ዘርፍ አገልግሎት ለማግኘት ይቸገራሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 40% የሚሆኑት ሴቶች እና ድሀ ሰዎች መሆናቸውን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡[3] ከዚህ አጠቃላይ ቁጥር ውስጥ ደግሞ ከግማሽ ቢሊዮን በላይ የሚልቀው ሕዝብ የሚገኘው በአፍሪካ ነው፡፡[4] ይህ ማለት እነዚህ ሰዎች በሚኖሩበት ሀገር ውስጥ አገልግሎት ለማግኘት አይችሉም ማለት ነው፡፡[5]

[1] ID4D 2022 Annual Report, available at https://documents1.worldbank.org/ p.13
[2] ዝኒ ከማሁ፡፡
[3] ዝኒ ከማሁ፡፡
[4] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 3
[5] ዝኒ ከማሁ፡፡

በኢትዮጵያ አብዛኛው ሰው የቀበሌ መታወቂያ ያለው ቢሆንም፣ የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ያልተደገፈ በመሆኑ ነዋሪው የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚያስገኛቸውን ትሩፋቶች ማግኘት አልቻለም፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሥር የዲጂታል መታወቂያን የሚያስተገብር የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ተቋቁሞ ላለፉት ሁለት ዓመታት በግንባታና በሙከራ ሂደት ላይ ቆይቷል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን ከተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰር የሙከራ ትግበራ ሥራዎችን በማከናወን ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ነዋሪዎችን መዝግቦ የዲጂታል መታወቂያ ባለቤት ለማድረግ ተችሏል፡፡ የኢትዮጵያን የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውጤታማ ለማድረግ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ አዋጅ ቁጥር 1284/2015 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል፡፡ ሕጉ ከሌሎች ሀገሮች ልምድ በመውሰድ የመታወቂያ ሥርዓትን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ እና በሌሎች ሀገራት የተከሰቱ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚጠቅሙ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡

በዚህ አጭር ጽሑፍ የመታወቂያ ሥርዓት በዓለም አቀፍ እና በሀገራችን ምን እንደሚመስል፣ በኢትዮጵያ ሊተገበር የታሰበው የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ሲተገበር የሚስገኛቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች ለመሳየት ጥረት ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱን አተገባበር እና አተገባበሩን ውጤታማ ለማድረግ በማለም አዋጁ ውስጥ የተካተቱ ሀሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ለማሳየት ይሞከራል፡፡

## 2. የመታወቂያ ሥርዓቶች

ሀገራት የተለያዩ የመታወቂያ ሥርዓቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ የመታወቂያ ሥርዓት በሁለት የሚከፈል ሲሆን እነዚህም መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት (Foundational ID system) እና አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ (Funcional ID system) ናቸው፡፡ ሁለቱን የመታወቂያ ሥርዓቶች ዘርዘር አድርገን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

### 2.1 መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት

መሠረታዊ መታወቂያ ማለት በመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት አማካኝነት የተሰጡ መታወቂያዎች የባለመታወቂያውን ማንነት በልዩነት በማረጋገጥ ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል የመታወቂያ ዓይነት ነው፡፡ በመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት መሠረት የሚሰጡ መታወቂያዎች ዋና አገልግሎታቸው የባለመታወቂያዎችን ማንነት ማረገገጥ ሲሆን፣ ማንነትን በማረጋገጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችንም ለማግኘትም ያስችላሉ፡፡ መሠረታዊ መታወቂያ በሌላ መልኩ ሕጋዊ መታወቂያ በመባል ይታወቃል፤ ይህን መታወቂያ የያዘ ሰው በየትኛውም ቦታ ራሱን ለማረጋገጥ መሠረታዊ መታወቂያውን መገልገል ይችላል ማለት ነው፡፡[6] መሠረታዊ መታወቂያ አንድን ሰው ከሌላ ሰው በልዩ ሁኔታ ለመለየት የሚያስችል የመታወቂያ ዓይነት ነው፤ ይህ ማለት አንድ ሰው የተለያዩ ማንነቶች ሊኖሩት አይችሉም፤ አንድ ማንነትም ከአንድ ሰው ውጭ የተለያዩ ሰዎች ማንነት ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡[7]

[6] World Bank, ID4D, Practitioners Guide, 2019, p.14.

[7] ዝኒ ከማሁ፡፡

መሠረታዊ መታወቂያ እንደ ብሔራዊ ወይም ዲጂታል መታወቂያ የሚያገለግል ሲሆን፣ ተፈፃሚነቱም ሀገር አቀፍ ነው፡፡ መሠረታዊ መታወቂያ በአንድ ሀገር ውስጥ በሁሉም ቦታ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጎ የሚሰጥ በመሆኑ በአብዛኛው በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ለመጭበርበር በማያመች መልኩ የሚዘጋጅ ነው፡፡

የመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት የተመዝጋቢዎችን የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃዎችን በመውሰድ ልዩ የመታወቂያ ቁጥር የሚሰጥበት ሥርዓት በመሆኑ ሰዎችን በልዩ ሁኔታ ለመለየት ከማስቻሉም በላይ፣ የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች የአገልግሎት ጠያቂዎችን ማንነት በቀላሉ ለመለየት ያስችላል፡፡[8] ይህም በአገልግሎት ጠያቂ እና አገልግሎት ሰጪ መካከል መተማመን እንዲኖር ያደርጋል፡፡[9] ከዚህም በተጨማሪ መሠረታዊ መታወቂያ የባለመታወቂያውን መሠረታዊ የሚባሉ መረጃዎችን የሚይዝ በመሆኑ የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች ለሚሰጧው አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች እንደ አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ ያገለግላል፡፡ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ የሚሰጡ አካላት እና ሌሎች የግለሰቦችን መረጃ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማግኘት የሚፈልጉ አካላት መረጃዎቹን ከግለሰቦች እንደአዲስ ከመሰብሰብ ይልቅ ከመሠረታዊ መታወቂያ መረጃ ቋት እንዲወስዱ፣ የመረጃ መጭበርበርን ለመቀነስ እና የተመዝጋቢዎችን መረጃ ለማስተዳደር የሚያስፈልግ ወጪ እና ጊዜን ለመቆጠብ ያስችላል፡፡

መሠረታዊ መታወቂያ የአንድን ሰው ማንነት በልዩ ሁኔታ ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ የግለሰቦችን የመታወቅ ሰብዓዊ መብት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ መንግሥትም ዜጎቹን የማወቅ ግዴታውን እንዲወጣ ያስችለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነዋሪዎች ከመንግሥት የሚፈልጉትን አገልግሎት በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችላቸው ሲሆን መንግሥትም ለነዋሪዎች መሠረታዊ አገልግሎት፣ የደህንነት እና ማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎት እና መሰል አገልግሎቶችን በመስጠት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ያስችለዋል፡፡ ይህ መታወቂያ ዘርፍ ተኮር አገልግሎቶችንም ለማግኘት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡ ለምሳሌ:- በብራዚል እና ፈረንሳይ የማኅበራዊ ጥበቃ አገልግሎት የሚሰጠው በመሠረታዊ መታወቂያ ብቻ ነው፡፡[10]

በሀገራችን መሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት ባይኖርም እንደ መሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት ሆኖ እያገለገለ ያለው የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ነው፡፡ መንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት እና ሌሎች ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሰነዶችን ለማግኘት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው የቀበሌ መታወቂያ ሲሆን፣ ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘትም ጥቅም ላይ የሚውለውም ይኸው የቀበሌ መታወቂያ ነው፡፡

### 2.2 አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት

በአገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት የሚሰጡ መታወቂያዎች ወይም ማንነትን ማረጋገጫ ሰነዶች የባለመታወቂያውን ማንነት ለማረጋገጥ የሚያገለግሎት ከተወሰነ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ወይም ከአንድ ዘርፍ ተግባር ጋር ብቻ በተያያዘ ሥርዓት ነው፤ በሌላ አገላለፅ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ ማለት የተወሰነ አገልግሎትን ብቻ ለማግኘት የሚያግዝ የመታወቂያ ዓይነት ነው፡፡

---

[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 15

[9] ዝኒ ከማሁ፡፡

[10] Identification Systems for Social Protection, Center for Social Development, 2016, p.16

መንግሥታዊም ሆነ የግሉ ዘርፍ የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት ተገልጋዮች ራሳቸውን ለማረጋገጥ መታወቂያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ለመምረጥ ወይም ለመመረጥ፣ የታክስ አገልግሎት ለማግኘት፣ ማኅበራዊ ጥበቃ ለማግኘት፣ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ለመንጓዝ፣ መኪና ለማሽከርከር እና መሰል አገልግሎቶችን ለማግኘት አስፈላጊውን መታወቂያ ማቅረብ የሚያስፈልግ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነት አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችሉ ዘርፍ ተኮር የሆኑ መታወቂያዎች አገልግሎት ተኮር መታወቂያ ተብለው ይታወቃሉ፡፡[11] የመንጃ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር፣ የጤና መድን ተጠቃሚነት መታወቂያ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መታወቂያ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ ዓይነቶች ሲሆኑ በኢትዮጵያም በዚሁ አግባብ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡[12]

አገልግሎት ተኮር መታወቂያ ከመሠረታዊ መታወቂያ የሚለይበት መሠረታዊ ባህርይ አለው፡፡ የመጀመሪያው አገልግሎት ተኮር መታወቂያ አገልገሎት ላይ የሚውለው አንድን አገልግሎት ለማግኘት ሲሆን መሠረታዊ መታወቂያ ግን ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች ለተሰጡበት ዓላማ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ጉዳይ እንደ ሕጋዊ መታወቂያ የሚወሰዱ አይደሉም፤ ነገር ግን የሚመለከተው የሕግ ማዕቀፍ እንደ ሕጋዊ መታወቂያ ሊወሰዱ እንደሚችሉ ከደነገገ በዚያው አግባብ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

አገልግሎት ተኮር መታወቂያ በሚመለከተው መሥሪያ ቤት ወይም ዘርፍ የሚሰጥ በመሆኑ ሀገር አቀፋዊነት ወይም ዘርፈ ብዙነት ባህርይ የለውም፤ አንድን አገልግሎት ወይም አንድን ዘርፍ በተመለከተ የሚሰጥ በመሆኑ የመታወቂያው ጥራት እና በሀሰት የመዘጋጀት ዕድሉ ሰፊ ሲሆን በአብዛኛው ሀገር አቀፍ በሆነ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አይደለም፡፡[13] አንዳንድ አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች የመሠረታዊ መታወቂያ ባህርይ ሊኖራቸው ቢችልም አብዛኛዎቹ አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች ግን አገልግሎት ተኮር ወይም ዘርፍ ተኮር ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አገልገግሎት ተኮር መታወቂያ በመሠረታዊ መታወቂያ ላይ ተመስርቶ ካልተዘጋጀ የመጭበርበር ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ ሀገራት እነዚህን መታወቂያዎች ከመሠረታዊ መታወቂያ ጋር እንዲተሳሰሩ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ማለት አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች በሚሰጡበት ጊዜ በመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንደ ግብዓት በመጠቀም አገልግሎት ላይ ማዋል ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቋማት ወይም ዘርፎች አገልግሎቶቻቸውን በመሠረታዊ መታወቂያ እንዲሰጡ ይመከራል፡፡ አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት በመሠረታዊ መታወቂያ የተመዘገቡ ሰዎች በድጋሚ ለአገልግሎት ተኮር መታወቂያ እንዲመዘገቡ ስለሚያስገድድ ለተጨማሪ ወጪ እና የጊዜ ብክነት የሚዳርግ ነው፡፡ ስለሆነም ሀገራት የአገልግሎት ተኮር መታወቂያ ሥርዓታቸውን ወደ መሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት እንዲቀይሩ ይመከራል፡፡[14]

[11] Identification for Development, available at https://id4d.worldbank.org/guide/types-id-systems

[12] ID4D Country Diagnostic, Ethiopia, 2017, p12

[13] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 6፣ ገጽ 14

[14] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 10፣ ገጽ 17

## 3. በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ መታወቂያ ሥርዓት

የኢትዮጵያን የመታወቂያ ሥርዓት ወደ ዘመናዊ መታወቂያ ሥርዓት ለማሸጋገር የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ የቆየ ቢሆንም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ውጤታማ ሥራ ማከናወን አልተቻለም። ስለሆነም አሁን በሀገራችን ያለው መደበኛው የመታወቂያ ሥርዓት የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ሲሆን ሌሎችም ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ መታወቂያዎች አሉ። የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት እና ሌሎች አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። እነርሱም ከላይ በክፍል 2 እንደተመለከተው መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት እና አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት ናቸው።

### 3.1 መሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት ስትጠቀምበት የቆየችው እና አሁንም እየተጠቀመችበት ያለው የመታወቂያ ሥርዓት የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ነው።[15] የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት አንድ ሰው የአንድ አካባቢ ነዋሪ ስለመሆኑ እና ማንነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል በታችኛው የመንግሥት መዋቅር አማካኝነት የሚሰጥ መታወቂያ ነው። የአብዛኛዎቹ ክልሎች አደረጃጀት በክልል፣ በወረዳ፣ በቀበሌ እና በከተማ አስተዳደሮች የተዋቀሩ ሲሆን፣[16] በተወሰኑ ክልሎች የብሔረሰቦች ዞን አደረጃጀት እንደ አንድ መዋቅር እውቅና ተሰጥቶት በክልል፣ በብሔረሰቦች ዞን፣ በወረዳዎች እና በቀበሌዎች የተዋቀረ መሆኑን ከሕገ-መንግሥቶቻቸው መረዳት ይቻላል።[17] በነዚህ የክልሎች አደረጃጀት እውቅና የተሰጠው የመጨረሻው እርከን ቀበሌ[18] ነው፤ በተግባር እንደሚታየው የቀበሌ መዋቅር በወረዳ የተቀረጹ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን የመተግበር፣ ለአካባቢው ሕግ ማውጣት ወይም እንዲወጣ ሀሰብ ማቅረብ፣ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ሥራዎችን ለመተግበር የሚያስችላቸው ዝርዝር የሆነ ዕቅድ እና ስትራቴጂ የማውጣት እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ልማታዊ እንቅስቃሴ ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ የማስተባበር ሥራ እንደሚሠሩ መረዳት ይቻላል። በቀበሌው ውስጥ ለሚኖር ነዋሪ መታወቂያ የሚሰጠውም በእነዚህ የቀበሌ መዋቅሮች ነው።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የቀበሌ መታወቂያ እንደመሠረታዊ መታወቂያ ተደርጎ ይወሰዳል፣ ምክንያቱም ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት እና ሌሎች አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎችን ለማግኘት ተቀባይነት ያለው የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ በመሆኑ ነው። ማንኛውም ሰው በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ሲንቀሳቀስ ማንነቱን ለማረጋገጥ የሚጠቀመው የቀበሌ መታወቂያ ነው። በአሁኑ ጊዜ የቀበሌ መታወቂያ እንደመሠረታዊ

[15] በአብዛኛው የሀገራችን ክፍል መደበኛ መታወቂያ የሚሰጠው በቀበሌ ስለሆነ የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት የሚለው ስያሜ የተሰጠው ቢሆንም አንዳንድ ቦታዎች ላይ በሌሎች አደረጃጀቶችም ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ የሚለው መዋቅር በወረዳ የተቀየረ በመሆኑ መታወቂያ የሚሰጠው በወረዳዎች ነው። በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ደግሞ መታወቂያ ከቀበሌ በታች ባሉ መዋቅሮች የሚሰጥበት ሁኔታ አለ። ስለሆነም የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት የሚለው ስያሜ መታወቂያ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የሚሰጠው በቀበሌ ብቻ እንደሆነ የሚያመለክት አይደለም።

[16] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 45፣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 43፣ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት፣ አንቀጽ 45

[17] የጋምቤላ ሕዝቦች ብሐየራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት፣ አንቀጽ 45

[18] ቀበሌ በሕግ እውቅና የተሰጠው የመጨረሻው አደረጃት ቢሆንም በተግባር ግን ከቀበሌ በታቸ ጎጥ እና መሰል አደረጃጀቶች አሉ።

መታወቂያ የሚያገለግል በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት በተግባር ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡[19]

የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት የራሱ የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ የሚሰጠው በታችኛው መዋቅር በመሆኑ እና በታችኛው መዋቅር የሚኖረው ሕብረተሰብ እርስ በእርሱ የሚተዋወቅ በመሆኑ መታወቂያውን ለማግኘት ቀላል ነው፡፡ የቀበሌ መታወቂያ እንደመሠረታዊ መታወቂያ የሚቆጠር በመሆኑ ማንነትን በማረጋገጥ የሚሰጡ በርካታ አገልግሎቶችን እና ሌሎች አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎችን ለማግኘትም ያስችላል፡፡[20] እንዲሁም መታወቂያውን ለማግኘት የሚከፈለው ክፍያ አነስተኛ በመሆኑ ለሁሉም ተደራሽ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ደካማ ጎኑን በሚመለከት፣ የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት እንደመሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት የሚቆጠር ቢሆንም የሚሰጠው በየአካባቢው በሚገኙ የመንግሥት መዋቅሮች በመሆኑ በአንድ አካባቢ የተሰጠ የቀበሌ መታወቂያ ሌሎች አካባቢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፡፡ የቀበሌ መታወቂያ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቢሆንም፣ በየመስተዳደሮቹ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት ያስችላል ማለት አይደለም፡፡ መታወቂያው ከተሰጠበት አካባቢ ውጭ ያሉ ሌሎች አካባቢዎች በቀበሌ መታወቂያ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስገድድ ሕግም ሆነ አሠራር የለም፡፡

ሌላው የቀበሌ መታወቂያ ድክመት በሀሰት ሊዘጋጅ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ አንድ አካባቢ ላይ የቀበሌ መታወቂያ ያገኘ ሰው በሌላ የሀገሪቱ ክፍል ሄዶ ሌላ የቀበሌ መታወቂያ እንዳያወጣ የሚከለክለው ሥርዓት የለም፡፡ የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት በቴክኖሎጂ የተሳሰረ ባለመሆኑ አንድ ሰው ከተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ የቀበሌ መታወቂያዎችን መውሰድ ይችላል፡፡ እንዲሁም መታወቂያው ራሱ ወደ ሀሰት ሊለወጥ ይችላል፣ በቀበሌ መታወቂያ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን በቀላሉ በሌሎች መረጃዎች መቀየር ስለሚቻል የቀበሌ መታወቂያ በቀላሉ ወደ ሀሰተኛ መታወቂያ የሚቀየር ነው፡፡[21] ስለሆነም በቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት አንድ ሰው በርካታ ማንነቶች ሊኖሩት ይችላል ማለት ነው፡፡

የቀበሌ መታወቂያ በየክልሎች መዋቅር የሚሰጥ በመሆኑ፣ በመታወቂያው ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ከቦታ ቦታ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ አልፎ አልፎም አላስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚይዝ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ተመራጭ የመታወቂያ ሥርዓት አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተሳሰረ ባለመሆኑ ለተለያዩ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች የተጋለጠ ከመሆኑም ባሻገር የዜጎችን የመታወቅ መብት በቀላሉ ለማረጋገጥ ስለማያስችል ዜጎች ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡ በመንግሥት በኩልም በርካታ ተግዳሮቶች እያጋጠሙ ሲሆን አግባብነት ያለው የልማት ዕቅድ ለማቀድ፣ ለዜጎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለመስጠት እና መሰል ተግባራትን ለማከናወን አላስቻለም፡፡ ስለሆነም የዲጂታል የመታወቂያ ሥርዓት በሀገሪቱ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

[19] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 12፣ ገጽ 5

[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 10

[21] ዝኒ ከማሁ፡፡

### 3.2 አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓት በኢትዮጵያ

ከቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ወይም መሠረታዊ መታወቂያ ሥርዓት በተጨማሪ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ የኢትዮጵያ የመታወቂያ ሥርዓት አካል ነው። በኢትዮጵያ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችሉ የመታወቂያ ዓይነቶች ያሉ አሉ። እነዚህም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ መንጃ ፈቃድ፣ የተለያዩ የክፍያ ካርዶች፣ የጤና መድን ተጠቃሚነት መታወቂያ፣ የሴፍትኔት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ መታወቂያ፣ የመንግሥት ሠራተኛ መታወቂያ፣ የፐብሊክ ትራንስፖርት ተጠቃሚነት መታወቂያ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ከላይ እንደተመለከትነው አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎችን ለማግኘት እንደማስረጃ የሚቀርበው ቀበሌ መታወቂያ ሲሆን፣ የቀበሌ መታወቂያ ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። ሀሰተኛ ወይም የተሳሳተ የቀበሌ መታወቂያን በመጠቀም የተገኘ አገልግሎት ተኮር መታወቂያ፣ በራሱ ትክክለኛ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም በሀገሪቱ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ የአገልግሎት ተኮር መታወቂያዎችን እውነተኛነት እና ትክክለኛነት ለማጠናከር ያስችላል። አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ ሥርዓትን በዘመናዊ መልኩ በተዘረጋ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት እየተጠናከረ እንዲሄዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## 4. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም ሀገራዊ ፋይዳ

በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለመዘርጋት በአሁኑ ጊዜ ወደ ሙሉ ትግበራ ተገብቷል። ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ እንደሀገር በርካታ ጠቀሜታዎች የሚኖሩት ሲሆን፣ እነዚህ ጠቀሜታዎች በኢኮኖሚው ዘርፍ፣ በማኅበራዊ ዘርፍ እና በፖለቲካው ዘርፍ የሚኖራቸው አስተዋፅኦ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.1 በኢኮኖሚ ዘርፍ

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ወደ ሕጋዊ መስመር በማምጣት ወይም በማስገባት፣ ሁሉም ሰው በኢኮኖሚ ሥርዓቱ ውስጥ እንዲሳተፍ በማድረግ እና መተማመንን የሚፈልጉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመቀየር ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።[22] በማኬንዚ ጥናት መሠረት ሀገራት ዲጂታል መታወቂያን ተግባራዊ ቢያደርጉ እስከ 2030 ድረስ በኢኮኖሚያቸው ላይ ከ3%-13% የሚደርስ ጂዲፒ እድገት እንደሚኖራቸው ያሳያል።[23] የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የፋይናንስ አካታችነትን (financial inclusion) በማሳደግ፤ መደበኛ የፋይናንስ ሥርዓት እያደገ እንዲሄድ እና ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል። የሥርዓቱ ተግባራዊ መደረግ የፋይናንስ ተቋማት ደንበኛ እንዲጨምር በማድረግ እና በፋይናንስ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል መተማመን እንዲፈጠር በማድረግ በ2025 የዓለም ኢኮኖሚ በ3.7 ትሪሊዮን ዶላር እንዲያድግ የማድረግ አቅም እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ።[24]

የተለያዩ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው የፋይናንስ ተቋማት እንቅስቃሴ በዲጂታል መታወቂያ ከመደገፉ በፊት እና በኋላ ከፍተኛ ልዩነት የሚያመጣ መሆኑን ነው። ለምሳሌ

---

[22] Digital Identification, A key to inclusive Growth, McKinsey Global Institute, 2019, p.19

[23] ዝኒ ከማሁ።

[24] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 40

በሕንድ የዲጂታል መታወቂያ ተግባራዊ ማድረግ ከተጀመረ በኂላ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት የፋይናንስ እንቅስቃሴ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ ሲገባ በዓመትም ሆነ በወር ስሌት ለኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ እገዛ ያደርጋል፡፡[25]

ይህ የመታወቂያ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፍ መሠረታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ጥናቶች ያመለክታሉ፤ በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ቢደረግ የፋይናንስ ተቋማት ደንበኛ ለመሆን እና የደንበኞችን ማንነት ለማረጋገጥ የሚወስደውን ጊዜ እና ወጪ በመቀነስ፣ በደንበኞች እና በፋይናንስ ተቋማት መካከል መተማመን እንዲኖር በማድረግ ደንበኞች የብድር እድል የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲጨምር በማድረግና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች በመፍጠር በ2030 እ.አ.አ 2 ቢሊዮን ዶላር ወደ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ እንዲገባ የሚስችል መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡[26] በኢትዮጵያ ከ65% በላይ የሚሆነው ሕዝብ ማለትም ወደ 41 ሚሊዮን የሚደርሰው ማኅበረሰብ ከፋይናንስ ሥርዓቱ የተገለለ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የባንክ አካውንት ለመክፈት የሚያስችል የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ አለመኖር፣ የፋይናንስ ተቋማት ከሕብረተሰቡ ሩቅ መሆናቸው፣ የባንክ አካውንት ለመክፈት የሚያስፈልጉ ወጪ እና መሰል ጉዳዮች ሲሆኑ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በሀገሪቱ ተግባራዊ ሲደረግ ከ65% ሕዝብ ቢያንስ 35%ቱን ሕዝብ ወደ ፋይናንስ ሥርዓቱ ማምጣት ያስችላል፡፡

አርሶ አደሩ የዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ ቢሆን በመሬት ላይ ያለውን መብት ለማረጋገጥ እገዛ የሚያደርግ የሚያስችለው ሲሆን፣ አርሶ አደሩ መሬቱን በቀጣይ በረጅም ጊዜ ወደ መደበኛ ኢንቨስትመንት ሥርዓት በማስገባት እና በመሳሰሉት በርካታ ጠቀሜታዎችን እንዲያገኝ ያስችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመሬት አስተዳደር ሥርዓቱንም ወደ ዲጂታል ሥርዓት በማስገባት ለአስተዳደራዊ እና መሰል ጉዳዮች የሚወጡ ወጪዎችን ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ከመሬት አስተዳደር አንፃር የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መደረጉ ለምሳሌ በሕንድ የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት እና መሰል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ እ.አ.አ በ2030 እስከ 0.9% ድረስ ለጂ.ዲ.ፒ እድገት አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ተገምቷል፡፡[27]

ማኬንዚ በ2019 እ.አ.አ. በኢትዮጵያ ባደረገው ጥናት መሠረት 25% የሚሆነው ሕዝብ በኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኛል፣ ለሥራ ከደረሰው የሰው ኃይል ውስጥ 85% የሚሆነው ሕዝብ ኢንተርኔት አያገኝም፤ እንዲሁም 65% የሚሆነው ሕዝብ ከዘመናዊ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ውጪ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 71% የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡[28] የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ቢደረግ በ2030 እ.አ.አ ከፋይናንስ ሥርዓት ውጪ የሆነውን ሕዝብ ወደ ፋይናንስ ሥርዓት በማምጣት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የመንግሥት የሥራ ሰዓት በመቆጠብ፣ የአርሶ አደሩን የመሬት ሥርዓት ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በማስገባት በጠቅላላ 12 ቢሊዮን ዶላር ሊያስገኝ እንደሚችልና ይህም በሀገሪቱ ጂ.ዲ.ፒ ላይ 6% እድገት እንደሚያመጣ ጥናቱ አመላክቷል፡፡[29]

---

[25] Ronald Abraham et al., State of Aadhaar report, 2017–18, ID insight, May 2018.

[26] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 22፣ ገጽ 40

[27] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 59

[28] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 71

[29] ዝኒ ከማሁ፡፡

ፍትሕ ሚኒስቴር በፋይናንስ ዘርፉ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ባደረገው ጥናት መሠረት በሦስት ዓመታት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሚሊዮን በላይ ገንዘብ ከባንኮች ብቻ እንደተጭበረበረ ያረጋገጠ ሲሆን[30] ይህ አሀዝ ምርመራ ከተደረገባቸው ወይም ሪፖርት ከተደረጉት ጉዳዮች የተሰወኑትን ብቻ በመውሰድ የተሠራ በመሆኑ በዝርዝር ጥናት ቢሠራ ቁጥሩ ከዚህም በላይ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ እነዚህ ወንጀሎች የተፈፀሙት የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ባለመኖሩ ሰዎች በቀላሉ ማንነታቸውን መቀያየር በመቻላቸው እና የፋይናንስ ተቋማት ደንበኞቻቸውን በቀላሉ ለማወቅ ባለመቻላቸው እንዲሁም በመሰል ምክንያቶች ነው፡፡

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን በማዘመን እና ገቢ እንዲጨምር በማድረግ፣ የፋይናነስ ተቋማት ተገልጋዮቻቸውን በቀላሉ መለየት እንዲችሉ በማድረግ በፋይናንስ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል መተማመን እንዲኖር በማድረግ፣ መደበኛ ያልሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ወደ መደበኛ ሥርዓት በማምጣት፣ የመንግሥትን የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በማዘመን፣ የሚባክን የሥራ ሰዓትን በመቀነስ እና የመሳሰሉትን ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የኢኮኖሚ ዘርፉን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

### 4.2 በማኅበራዊ ዘርፍ

በሀገራችን ሀገር አቀፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ እንደትልቅ ጉድለት የሚታይ ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ባለመኖሩ አንድ አካባቢ ላይ ወንጀል የፈፀመ ሰው፣ ስሙን ቀይሮ ወደ ሌላ የሀገሪቱ ክፍል ሄዶ መኖር የተለመደ እና በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ እንደትልቅ ተግዳሮት የሚታይ ነው፡፡ ሌላው የዚህ ሥርዓት ክፍተት በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚንፀባረቀው ደጋጋሚ ወንጀለኞችን ለመለየት አለመቻሉ ነው፡፡ አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሞ ከተፈረደበትና ታስሮ ከተፈታ በኋላ ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ሲመጣ ለመለየት የሚያስችል ሥርዓት በፖሊስም ሆነ በማረሚያ ቤቶች የተዘረጋው ሥርዓት ውጤታማ በመሆን ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ እያንዳንዱ ተጠርጣሪም ሆነ ታራሚ ወደ ፍትሕ አካላት ሲቀርብ ከዚህ በፊት ወንጀል የፈፀመ ስለመሆን/አለመሆኑ ውጤታማ በሆነ መንገድ መለየት አይቻልም፣ ይህም የፍትሕ ሥርዓቱ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ስለሆነም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ቢደረግ ወንጀልን በመቀነስ እና በደጋጋሚዎች ላይ ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን በማስቻል ረገድ ለፍትሕ ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የሀገርን እና የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃርም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት ሀገራዊና የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ደህንነት ለማረጋገጥ፣ የድንበር ሸግግር ቁጥጥር ለማገዝ እንዲሁም በሕግ ለተፈቀዱ የደህንነት ሥራዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ በማገልገል ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆኑ የበርካታ ሀገራት ልምድ ያሳየናል፡፡ የደህንነት ሥራ ከሰዎች ማንነት ጋር የሚገናኝ በመሆኑ፣ ሰዎችን በልዩነት ለመለየት የሚያስችል ሥርዓት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከትራንስፖርት ዘርፉ ጋር በተያያዘም የትራንስፖርት ዘርፉን ለማዘመን፣ ስማርት የትራንስፖርትን አገልግሎት ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና ከመንጃ ፈቃድ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ጠቀሜታው እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

[30] በባንኮች ላይ የሚፈጸሙ የማጭበርበር ወንጀሎች መንስኤዎቻቸውና የአፈፃፀም ዘዴዎቻቸው፣ ፍትሕ ሚኒስቴር 2014፣ ገፅ 22.

ከሥራና ፈጠራ ጋር በተያያዘ ማኬንዚ በ2019 በኢትዮጵያ ባደረገው ጥናት ለሥራ ከደረሰው የሰው ኃይል ውስጥ 9 ሚሊዮኑ በአግባቡ ሥራውን የማይሠራ (Inactive) ሲሆን 3 ሚሊዮን ደግሞ ሥራ አጥ ነው፡፡[31] የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ቢደረግ ለበርካታ ሥራ አጥ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚቻል ሲሆን፣ የሥራ አጥ ቁጥርን ለማወቅ፣ አላግባብ የሥራ እድል ተጠቃሚነትን ለመከላከል፣ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ የሥራ ፈጠራን (entrepreneurship) ለማጎልበት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሥራ ፈጠራን (technology start-up) ለማበረታታት እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ለማከናወን የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አስፈላጊ ነው፡፡

የግብርናው ዘርፍ ከነዋሪዎች ጋር በተያያዘ በየዓመቱ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ያንቀሳቅሳል፡፡ ለምሳሌ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ እና መሰል ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ ግብዓቶች በየዓመቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እየተገዙ ለተጠቃሚዎች የሚከፋፈሉ ሲሆን፣ ነገር ግን በትክክል ለተባለው ሰው ስለመድረስ አለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት የለም፡፡ አሁን ያለው የመታወቂያ ሥርዓት አንድ አካባቢ እነዚህን ግብዓቶች የወሰደ ሰው ሌላ አካባቢ ሄዶ ድጋሚ ሌላ ስም በመጠቀም ቢቀበል ለመለየት የሚያስችል አይደለም፡፡ በሀገሪቱ በርካታ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ያሉ ቢሆንም ይህ የሴፍቲኔት አገልግሎት በትክክል ለሚመለከታቸው አካላት እየደደረሰ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡

ዘመናዊ የመታወቂያ ሥርዓት ባለመኖሩ በሀገሪቱ በትክክል ስንት የመንግሥት ሠራተኞች አሉ የሚለውን መመለስ አይቻልም፡፡ ስለሆነም የመንግሥት ሠራተኛ ቁጥር በትክክል ለማወቅ፣ ትክክለኛ የትምህርት ማስረጃ ያላቸውን የመንግሥት ሠራተኞች ሀሰተኛ ሰነድ ከሚጠቀሙ ለመለየት፣ ለምሳሌ የመንጃ ፣ ሕገወጥ ደሞዝና ክፍያዎች ጋር የተያያዙ ማጭበርበሮችን ለማስቀረት የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በከተማ ልማት ዘርፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ባለመኖሩ በርካታ ችግሮች እያስከተለ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ በሀገሪቱ ስንት የከተማ ነዋሪ አለ የሚለውን ማወቅ ካልተቻለ ለነዋሪው የሚያስፈልገውን መሠረተ ልማት ማቅረብ አይቻልም፣ የሚመለከታቸው ተቋማትም አግባብነት ያለውን ዕቅድ ማዘጋጀት አይችሉም፡፡ ለምሳሌ የቤት አቅርቦት ላይ ለመሥራት የቤት ፈላጊዎችን ቁጥር በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል፤ በጤናው ዘርፍ አጠቃላይ የሀገሪቱን ነዋሪ ቁጥር ማወቅ አግባብነት ያለውን የጤና አገልግሎት ለማቅረብ አጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የጤና ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በትትክል በማወቅ ፍትሐዊ የሆነ አገልግሎት ለማቅረብ፣ የጤናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ለማዘመን፣ ትክክለኛ የጤና እቅድ ለማቀድና ለመፈጸም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የማይተካ ሚና አለው፡፡

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ በትምህርት ዘርፉ ላይ በርካታ ሕገ-ወጥ ተግባራት እንዲፈፀሙ አስችሏል፡፡ ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ መጠቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በሀገሪቱ የሚገኙ ትክክለኛ የተማሪዎችን እና የመምህራንን ቁጥር ለማወቅ፣ የፈተና ስርቆትን ለመከላከል እና ለመሳሰሉት ሥርዓቱ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የዲጂታል ክፍያዎችንና የኤሌክትሮኒክስ ግብይትን ተግባራዊ ለማድረግ፣

[31] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 22፣ ገጽ 71

የሳይበር ደህንነት ጥበቃ ለማጠናከር፣ የቴሌኮም አገልግሎትን ለማዘመን፣ ተንቀሳቃሽ የገንዘብ ዝውውርን (mobile money) ለማዘመን እና የመሳሰሉት በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ከሚኖሩት ጠቀሜታዎች የተወሰኑት ናቸው።

በአጠቃላይ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሀገራዊ ልማትን በአግባቡ ለማቀድ፤ ምጣኔ ሃብታዊ ሽግግር ለመፍጠር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ፖሊሲዎች ሲቀረጹ እና ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን እና አካታች ያለመሆን ችግርን በቀላሉ በመለየትና በመቅረፍ የሀብት ብክነትን በመቀነስ በነዋሪዎች መካከል ፍትሐዊነትን ለማስፈን እና ከወንጀል ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

### 4.3 በፖለቲካ ዘርፍ

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በፖለቲካው ዘርፍ በርካታ የሆኑ ጠቀሜታዎች አሉት። በየጊዜው የሚደረጉ ምርጫዎች ላይ መራጮችንና ተመራጮችን የመለየት ሥራ፣ መራጮችንና ተመራጮችን የመመዝገብ ሥራ በርካታ ሚሊዮን ገንዘብ የሚያስወጣ ተግባር ነው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሕጋዊነት ተመዝግበው በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ 20 የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በክልሎች የሚንቀሳቀሱ ደግሞ 41፣ በአጠቃላይ 61 የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲሆኑ[32] እነዚህ ፓርቲዎች በርካታ አመራሮች እና አባላት አሏቸው። ስለሆነም የመራጮችን እና ተመራጮችን መረጃ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አንድ ጊዜ በመመዝገብ እና በየጊዜው የሚደረግ ምዝገባን በማስቀረት የሚባክን ጊዜ እና ገንዘብ መቆጠብ ይቻላል።

በየክልሎች የሚኖሩ ነዋሪዎችን መረጃ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመመዝገብ እና ትክክለኛ መረጃ እንዲኖር በማድረግ በየክልሎቹ የሚነሱ ፖለቲካዊ አንድምታ ያላቸውን ጥያቄዎች መቀነስ ይቻላል።[33] የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ሲደረግ የነዋሪዎችን ማንነት መሠረት አድርጎ የሚፈጸሙ አድሎአዊ አሠራሮችን እና አልፎ አልፎም ጥቃቶችን በማስቀረት የፖለቲካ ሥርዓቱ የተረጋጋ እንዲሆን እና ብሔር ተኮር የሆኑ ጉዳዮችን በአጀንዳነት እንዳይነሱ በማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል።

## 5. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ የሕግ ማዕቀፍና አተገባበር

መግቢያው ላይ እንደተመለከተው በኢትየጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለመዘርጋት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሥር የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ተቋቁሞ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን የሙከራ ትግበራውን በማጠናቀቅ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል። የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በብዙ ሀገራት ፈተና የሚሆነው አተገባበሩ ነው። ሀገራት የየራሳቸውን የአተገባበር ሥርዓት የሚከተሉ ሲሆን በሀገራችንም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረገው ወይም ተግባራዊ ለማድረግ የታሰበው እንዴት ነው የሚለው እስከ አሁን ደረስ በአብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል ግልፅ እንደልሆነ መገንዘብ ይቻላል።

---

32 ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተገኘ ማስረጃ

33 በየክልሎቹ የሚገኙ ልሂቃን መንግሥት ሆነ ብሎ የአንዳንድ ክልሎችን ሕዝብ ቁጥር አሳንሶ እንደመዘገበ የሌላውን ክልል ሕዝብ ቁጥር ደግሞ ከፍ አድርጎ እንደመዘገበ የሚያነሱ ሲሆን ይህም ለየክልሎቹ ከሚሰጥ ከበጀት ድልድል እና መሰል ጉዳዮች ጋር የሚያያዝ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ይገልፃሉ።

አንዳንድ ሰዎች ዲጂታል መታወቂያ ማለት አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎችን ጨምሮ ሌሎች ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሰነዶችን በመተካት ሌሎቹ ከአገልግሎት ውጭ የሚሆኑበትን ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ አተገባበሩንም በተመለከተ ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ክልል ላለው ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ይህን መታወቂያ እንዴት ነው ማዳረስ የሚቻለው የሚለውን የሚጠይቁ አሉ፡፡ ስለሆነም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን በምን አግባብ ለመተግበር እንደታሰበ ለመገንዘብ በአዋጁ ላይ ከአተገባበሩ ጋር በተያያዘ የተካተቱ ድንጋጌዎችንና መሰል ጉዳዮችን መመልከት ያስፈልጋል፡፡

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ አተገባበሩን የሚደግፍ የሕግ ማዕቀፍ (legal framework) መኖር ነው፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አተገባበር በሕግ ካልተደገፈ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፣ ምክንያቱም በመታወቂያው የሚገለገሉ ሰዎች ምን መብት እና ጥቅም እንደሚያስገኝላቸው እና መታወቂያውን እንደ ሕጋዊ ሰነድ ለመቀበል ፈቃደኛ የማይሆኑ አካላት በሚኖሩበት ጊዜ ተጠያቂነታቸው እስከምን ድረስ እንደሆነ አስገዳጅ የሕግ ማዕቀፍ መኖር አለበት፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱን ማን ያስተባብረዋል፣ አጠቃላይ ሥርዓቱ ከሌሎች መታወቂያን ከሚመለከቱ ሥርዓቶች ጋር የሚኖረው መስተጋብር እንዴት እንደሆነ እና መሰል ጉዳዮች በሕግ ምላሽ ማግኘት አለባቸው፡፡

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ አዋጁ ከሌሎች ሀገሮች የመታወቂያ ሥርዓትን የሚመለከቱ ሕጎች ዘግየት ብሎ የወጣ በመሆኑ በሌሎች ሀገራት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከአተገባበሩ ጋር የሚያያዙና ከሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ የተካተቱ የተወሰኑ ነጥቦችን እንደሚከተለው ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

### 5.1 የሕጉ ዓላማ

የዲጂታል መታወቂያን የሚመለከቱ ሕጎች የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ ዓላማ ምን እንደሆነ በግልፅ የሚያመለክት ዓላማ እንዲኖራቸው ይመከራል፡፡ በሕግ አረቃቀቅ ዘዴ አንድ ሕግ መግቢያ የሚኖረው ከሆነ መግቢያው የሕጉንም ዓላማ የሚያካትት በመሆኑ ዓላማ ለብቻው መደንገግ ላያስፈልግ ይችላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሕጎች በተለይም ተግባራዊ ሲደረጉ ብዥታን የሚፈጥሩ ሕጎች በሆኑ ጊዜ በልዩ ሁኔታ ዓላማ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚመከር የሕግ አረቃቀቅ ዘዴ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ዓላማ እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን ይህም ሥርዓቱን በታሰበው ዓላማ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ሕጉ ዓላማዎቹን የሚገልጽ ሲሆን እነዚህም፣ ነዋሪዎች በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ሲንቀሳቀሱ በቀላሉ የመታወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥ በማድረግ ለሰብአዊ መብቶቾ አከባበር እና ለመልካም አስተዳደር መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ፣ አገልግሎት ማግኘት የሚፈልጉ ግለሰቦችን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት በአገልግሎት ሰጪ እና አገልግሎት ተቀባይ መካከል እምነት እንዲጎለብት ማድረግ፣ ሕገ-ወጥ ተግባራትን መከላከል፣ ሀገር አቀፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በማደራጀት ሀገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶች ሲቀረጹ እና የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን መቅረፍ፣ በዚህም የሀብት ብክነትን መቀነስ እና አካታችነትን ማጎልበት እና የነዋሪዎችን የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ለሌሎች መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ላልሆኑ አካላት የመታወቂያ ሥርዓት መረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገል፣ አገልግሎት ተኮር የሆኑ

የመታወቂያ ሥርዓቶች ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት እንዲሸጋገሩ ማጠናከር የሚሉ ናቸው፡፡[34]

በሕጉ እነዚህ ዓላማዎች መካተታቸው ሥርዓቱ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ በነዚህ ዓላማዎች ቅኝት ተግባራዊ ለማድረግ እንደ አተገባበር ፍኖተ ካርታ የሚያገለግሉ ናቸው፤ ስለ ስለኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ዓላማ መረዳት ለሚፈልጉ አካላትም እንደመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 5.2 የሕጉ የተመጠነ መረጃ ሥርዓት ባህርይ

በዲጂታል ሥርዓት ውስጥ መካተት ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የተመጠነ መረጃ ሥርዓት ነው፡፡ ለዲጂታል መታወቂያ ተመዝጋቢዎች መታወቂያውን ለመስጠት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተመጠኑ አነስተኛ መሆን እንዳለባቸው ተቀባይነት ያገኘ መርህ ነው፡፡ በአንዳንድ ሀገራት ልምድ እንደታየው የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት በርካታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ ሲሆን ይህም ሥራቸውን አንዳወሳሰበባቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በጋና የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ከ30 በላይ መረጃዎች ይሰበሰባሉ፤ ከነዚህ መረጃዎች ውስጥ የዐይን ቀለም፣ ቁመት፣ የጋብቻ ሁኔታ እና ሌሎች የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ምንም ጥቅም የሌላቸው መረጃዎች ይገኙበታል፡፡[35]

የተመጠነ መረጃ ሥርዓት መነሻ የሚያደርገው ዲጂታል መታወቂያ የሚሰጠው አካል መሰብሰብ ያለበት መታወቂያውን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መረጃዎችን ብቻ መሆን አለበት የሚለውን መርህ ነው፡፡ የዲጂታል መታወቂያ የሚሰጠው አካል በርካታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ባደረገ ቁጥር የዲጂታል መታወቂያ አሰጣጥ ፕሮጀክቶችን ዕድሜ ያራዝማል፤ አንዳንድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እውነተኝነታቸውን ማረጋገጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ እነሱን ለማረጋገጥ የሚወስደው ጊዜ ረጅም ይሆናል፣ ይህም ሥራን ያከብዳል የሚሉ ምክንያቶች ይቀርባሉ፡፡

የግለሰቦችን መረጃ መሰብሰብ በራሱ ከሰዓአዊ መብት አንፃር አግባብነት የሌለው ቢሆንም መታወቂያ እንዲያገኙ ለማድረግ እና በመታወቂያውም የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ መረጃቸውን መሰብሰብ በሕግ የተፈቀደ ተግባር ነው፤ እንዲያም ሆኖ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተመጠኑ እና መታወቂያውን ለመስጠት የሚያስችሉ ብቻ መሆን አለባቸው፣ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች በላይ መሰብሰብ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የተመጠነ መረጃ ሥርዓት፣ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የተመጠኑ ወይም አነስተኛ መሆን አለባቸው ከሚለው በተጨማሪ ምስጢራዊ እና ከሰዎች ግላዊ ማንነት ጋር የሚገናኙ መረጃዎች በተቻለ መጠን ሲሰበሰቡ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት እና አስፈላጊ የሆኑት ብቻ እንዲሰበሰቡ ማድረግ የሚመክር መርህ ነው፡፡ ለምሳሌ የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ባዮሜትሪክ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን በተቻለ መጠን የጣት አሻራ፣ የሁለት ዓይን ብሌኖችና የፊት ገፅታ ፎቶ ከተወሰደ ዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት በቂ ነው፡፡

ነገር ግን በአንዳንድ ሀገሮች ከዚህም የዘለለ የባዮሜትሪክ መረጃዎችን የሚሰበስቡበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ በኬንያ ከነዚህ መረጃዎች በተጨማሪ የጆሮ አሻራ እና የድምፅ

---

[34] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 1284/2015፣ አንቀጽ 5

[35] Towards the evaluation of socio-Digital Ecosystem in Africa, Comparative analysis of findings from ten countries, Center for internet and society and research ICT Africa, 2021, p. 31.

ሞገድ ጭምር ይሰበስባል፡፡[36] በሌሎች ሀገሮች ደግሞ ብሔር እና መሰል ጥንቃቄ የሚፈልጉ የዲሞግራፊክ መረጃዎችም ይሰበስባሉ፡፡ የነዚህ መረጃዎች መሰብሰብ ግለሰቦችን ለአድሎ እና ለአደጋ የማጋለጥ፣ የግለሰቦችን ሰብአዊ መብትን የመጣስ እና ሥራውን የማወሳሰብ ውጤት ይኖረዋል፡፡

ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት አዋጁ የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት መወሰድ ያለባቸው የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃዎች አነስተኛ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በአዋጁ መሠረት የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት መሰብሰብ ያለባቸው መረጃዎቸ የዲሞግራፊክ መረጃዎች ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም፣ (ወይም በዚህ መልክ የተደራጀ ሕጋዊ ስም ለሌለው ተመዝጋቢ ሕጋዊ የሆነ ስያሜ ወይም ተመዝጋቢው በአካባቢው ማኅበረሰብ የሚጠራበት ስም፣) ዜግነት፣ የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመት፣ ፆታ እና የመኖሪያ አድራሻ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የእናት ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም ኢሜይልና የፖስታ አድራሻ ሊካካቱ እንደሚችሉ አዋጁ ይደነግጋል፡፡

የባዮሜትሪክ መረጃን በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች እንደሚሰበሰቡ አዋጁ ደንግጓል፡፡[37] ከዚህም በተጨማሪ ለዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ነዋሪዎችን በልዩ ሁኔታ ለመለየት የግድ የሚያስፈልጉና ሥርዓቱን በቀጥታ የሚከተሉ ካልሆኑ በስተቀር ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ ክልክል መሆኑ በሕጉ በግልፅ ተደንግጓል፡፡[38] ብሔር፣ የዘረመል ሁኔታ፣ የአካላዊ ወይም የአዕምሯዊ ጤንነት ወይም ሁኔታን፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ሃይማኖት ወይም ሌላ ሃይማኖት ነክ አስተሳሰብ፣ የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀል፤ የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀልን አስመልክቶ የተካሄዱ ሂደቶች፣ እነዚህ ሂደቶች የተጠናቀቁበት መደምደሚያ ወይም በሂደቶቹ ዙሪያ ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ እና ሌሎች በሚመለከተው አካል የሚወሰኑ መረጃዎች ጥንቃቄ የሚፈልጉ የግል መረጃዎች በመሆናቸው፣ በምንም መልኩ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ መሰብሰብ የሌለባቸው መሆኑን ሕጉ በግልፅ ደንግጓል፡፡[39]

በተግባር እንደሚታየው የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የሚሰበሰቡ የባዮሜትሪክ መረጃዎች አሥር የጣት አሻራዎች፣ የፊት ገፅታ ፎቶ እና የሁለት ዓይን ብሌን ብቻ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አነስተኛ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ሕጉ መደንገጉ ፕሮጀክቱን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚኖረው ሲሆን፣ ከሰብዓዊ መብት አጠባበቅ አንፃርም የሚነሱ ትችቶችን ለማስቀረት ይጠቅማል፡፡

### 5.3 በሕጉ አተገባበር ረገድ የመረጃ አጠባበቅ ሥርዓት

ሌላው በዲጂታል መታወቂያ አተገባበር ሥርዓት ብዙ ጊዜ ትችት የሚቀርብበት መታወቂያውን ለመስጠት ከግለሰቦች የሚሰበሰብ መረጃ አጠባበቅን በተመለከተ ነው፡፡ ግለሰቦች የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የሚሰጡት መረጃ በተለይም የባዮሜትሪክ መረጃ በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ ያለበት ሲሆን ግለሰቡ ካልፈቀደ እና በሕግ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር ለማንም ሦስተኛ ወገን የሚሰጥ መሆን የለበትም፡፡ የመረጃ አጠባበቅ ሥርዓት በሕግ በግልፅ መደንገግ ያለበት ከመሆኑ ባሻገር መረጃውን ለመያዝ

[36] ዝኒ ከማሁ፡፡
[37] የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ፣ ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 34፣ አንቀጽ 8
[38] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 16
[39] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2(18) እና 9(3)

የሚያገለግለው ዳታ ማዕከልም በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መገንባት አለበት። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመረጃ አጠባበቅን በተመለከተ አዋጁ ግልፅ ድንጋጌ አለው።

በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የተሰበሰበ የማንኛውም የተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ባለቤት ተመዝጋቢው በመሆኑ፤ በማንኛውም የዲጂታል መታወቂያ አሠራር ሥርዓት ውስጥ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረጉ የማረጋገጥ ተግባራት በተመዝጋቢው ፈቃድ መደረግ እንዳለባቸው፣ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚገቡ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመመዝገብ፣ በማረጋገጥ እና ይዞ በማቆየት ሂደት ባሉ ተግባራት ውስጥ የተመዝጋቢ መረጃዎች ምስጢራዊነት የተጠበቀ እንዲሆን መዝጋቢው አካል እና ተቋሙ ማረጋገጥ እንዳለባቸው፣ ማንኛውም ተመዝጋቢ ፈቃዱን በግልጽ ሳይሰጥ በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የተመዘገቡ የግል መረጃዎችን መውሰድ፣ ማሰራጨት፣ ማተም፣ መጠቀም፣ መረጃውን መስጠት ወይም ቅጂውን ለሦስተኛ ወገኖች ወይም አካላት መስጠት ወይም ይፋ ማድረግ የተከለከለ መሆኑን ሕጉ ደንግጓል።[40] ሕጉ የመረጃ አጠባበቅ ሥርዓትን የበለጠ ለማጠናከር በማሰብ የዲጂታል መታወቂያ ተቋም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የግል መረጃን በአስተማማኝነት የሚይዝ ጠንካራ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚለዋወጡ የዲጂታል መታወቂያ መረጃዎችን የማዘመን፣ እንደገና የማረጋገጥ፣ የማደስ፣ በጊዜያዊነት የመቆለፍ ወይም የመሻር ሥራዎችን እንደሚሠራ ተደንግጓል።[41]

የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት የተሰበሰቡ መረጃዎች በመርህ ደረጃ ለማንም የማይሰጡ ወይም የማይጋሩ ሲሆን በልዩ ሁኔታ ግን በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሊሰጡ እንደሚችሉ ሕጉ ይደነግጋል።[42] ይህ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ለፍትሕ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በፍትሕ አካላት ሲፈለጉ እና ለደህንነት ሥራ በሚፈለጉበት ጊዜ ትብብር የማድረግን አሠራር በሕግ ማዕቀፍ ግልፅ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው።

## 5.4 የመረጃ ሥርዓቱ ተግባራዊነት አግላይ እንዳይሆን የሚደረግ ጥንቃቄ

የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተግባራዊ ካደረጉ ሀገራት ልምድ እንደታየው፣ የዲጂታል መታወቂያ ተግባራዊ ሲደረግ ሕብረተሰቡ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና የሚፈጠርበት ሁኔታ አለ። ይህ ጫና በሁለት ምክንያቶች የሚመጣ ሲሆን አንደኛው የዲጂታል መታወቂያ ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት ግዴታ ሆኖ ሲተገበር ነው፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የሚቀመጡ መስፈርቶች እና ሂደት ጥብቅ ሲሆኑ ነው። ለምሳሌ በናይጀሪያ ማንኛውንም መሠረታዊ አገልግሎት የሚሰጠው የዲጂታል መታወቂያ ይዘው ለሚቀርቡ ሰዎች እንደሆነ በሕግ የተደነገገ ሲሆን ይህ አቀራረብ መታወቂያው የሌላቸው ሰዎች የመንግሥት አገልግሎት በማግኘት ረገድ እክል እንዲገጥማቸው በማድረግ በነዋሪዎች መካከል ልዩነቶችን ይፈጥራል።[43]

ይህ አግላይነት የዲጂታል መታወቂያን እንደግዴታ አድረጎ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን የዲጂታል መታወቂያ የሚገኝበት ሂደት ውስብስብ እና ከባድ ከሆነ ሰዎች መታወቂያውን

---

[40] ዝኒ ከማሁ።

[41] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 17

[42] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 17(5)

[43] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 36፣ ገጽ 31

[43] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 34፣ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ፣ አንቀጽ 33

በቀላሉ ስለማያገኙ ለአገልግሎት እጦት ይዳረጋሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በኡጋንዳ የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የጣት አሻራ መስጠት የግዴታ ሆኖ የተቀመጠ በመሆኑ በአካል ጉዳተኝነት እና በዕድሜ መግፋት ምክንያት የጣት አሻራ መስጠት የማይችሉ ሰዎች መታወቂያውን ስለሚያገኙበት አማራጭ አልተቀመጠም፤ ይህም ለመገለል ዳርጓዋል፡፡[44] እንዲሁም በዚምባቡዌ የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የልደት የምስክር ወረቀት ማቅረብ ግዴታ በመሆኑ በአንድ ወቅት በሦስት ክልሎች ብቻ ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች መታወቂያውን ማግኘት አልቻሉም፤[45] በመሆኑም የመንግሥት አገልግሎት በማግኘት ረገድ ለችግር ተዳርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሕግ እነዚህን ችግሮች ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን አካቷል፤ በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ነጥብ አገልግሎት ለማግኘት የዲጂታል መታወቂያ መያዝ በመርህ ደረጃ አስገዳጅ አለመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ተጠቃሚ አካል ለነዋሪው ለሚሰጠው አገልግሎት የዲጂታል መታወቂያን እንደ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የሚያደርግ አሠራር በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ መዘርጋት ይችላል፤[46] እንዲሁም ማንኛውም ተመዝጋቢ የዲጂታል መታወቂያ ላይ የተመሠረተ የማረጋገጥ አገልግሎት ለማግኘት ልዩ ቁጥር ወይም ልዩ ቁጥሩን የያዘ የዲጂታል መታወቂያ ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡[47]

ነዋሪዎች የዲጂታል መታወቂያ የሚያገኙበትን ሥርዓት አዋጁ ሲደነግግ፣ አጠቃላይ አቀራረቡ ነዋሪዎች መታወቂያ እንዲያገኙ በሚያበረታታ መልኩ ነው፡፡ ማንኛውም ነዋሪ ማንነቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ይዞ በመቅረብ የዲጂታል መታወቂያ መውሰድ የሚችል ሲሆን፣ ማንነቱን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ሰነድ ከሌለው ደግሞ ምስክር ይዞ በመቅረብ መመዝገብ ይችላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የባዮሜትሪክ መረጃ መስጠት የግዴታ መሆኑን ከደነገገ በኋላ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ተመዝጋቢው ሌሎች ባዮሜትሪክ መረጃ መስጠት አለመቻሉ በመዝጋቢው አካል ከተረጋገጠ፣ የፊት ገፅታ ፎቶግራፍ ብቻ በመመዝገብ ዲጂታል መታወቂያ ሊሰጥ እንደሚችል፣ እንዲሁም በጤና ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት መዝጋቢው አካል ምዝገባ ወደ ሚያደርግበት ቦታ መምጣት የማይችሉ ተመዝጋቢዎችን ባሉበት ቦታ ወይም አመቺ በሆነ ቦታ በመገኘት መዝጋቢው አካል ምዝገባ ሊያደርግ እንደሚችል እና ዝርዝሩ በመመሪያ እንደሚወሰን ተደንግጓል፡፡[48]

ሌላው የዲጂታል መታወቂያ የሌለው ሰው አገልግሎት ከማግኘት እንዳይታገድ፣ ዋና ዋና አገልግሎት ሰጪዎች ዲጂታል መታወቂያ የሌላቸው ተመዝጋቢዎች ለመገልገል በሚመጡበት ጊዜ፣ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ በማካሄድ እና መታወቂያውን እዚያው በመስጠት አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ በተግባር ለማመቻቸት እየተሠራ ይገኛል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች በመመልከት ሕጉ ነዋሪዎች መታወቂያ እንዲያገኙ በርካታ አማራጮችን የሰጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ ይህም አጠቃላይ ሥርዓቱ አግላይ እንዳይሆን በሕጉ ታሳቢ የተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

[44] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 36፣ ገጽ 34
[45] ዝኒ ከማሁ፡፡
[46] ከላይ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 34፣ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ፣ አንቀጽ 14(1)
[47] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 15(5)
[48] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 8

## 6. በዲጂታል መታወቂያ ትግበራ ሂደት የምዝገባ ሥርዓት

ከዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት አተገባበር ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነጥብ ለዚህ ሁሉ ከ120 ሚሊዮን በላይ ለሆነ ሕዝብ እንዴት ነው የዲጂታል መታወቂያ ማዳረስ የሚቻለው የሚለው ነው። የምዝገባ ሥርዓቱን በተመለከተ ሀገራት የተለያዩ አካሄዶችን በመጠቀም ምዝገባ ያካሂዳሉ። በእኛ ሀገር ለማካሄድ የታሰበው የምዝገባ ሥርዓት በሦስት መንገድ ሲሆን እነርሱም፣ አንደኛ፣ የዲጂታል መታወቂያ ተቋም በራሱ የሚያካሂደው የምዝገባ ሥርዓት፣ ሁለተኛ፣ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት በሚሰጡ አካላት (ለምሳሌ ግብር አስገቢ ተቋማት፣ ባንኮች ወዘተ …) በኩል የሚደረግ ምዝገባ ወይም ተጠቃሚዎችን መሠረት ያደረገ የምዝገባ ሥርዓት (use case approach) ወይም የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ይህንን ምዝገባ እንዲያካሂዱ የሚደረግበት አሠራር (outsourcing to NIDP partners)፣ ሦስተኛ፣ ሌሎች አካላት ከተቋሙ ፈቃድ ወስደውና ከተመዝጋቢዎች መጠነኛ ክፍያዎችን በማስከፈል የሚያደርጉት የምዝገባ ሥርዓት ነው።[49]

የዲጂታል መታወቂያ ተቋሙ የሚያካሂደው ምዝገባ (Fayda Centre Approach) ማለት ተቋሙ ራሱ የምዝገባ መሣሪያዎችን ገዝቶ፣ ባለሙያዎችን ቀጥሮ እና የምዝገባ ማዕከላትን አመቻችቶ የሚያካሂደው ምዝገባ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በርካታ ነዋሪዎች በዚህ የምዝገባ ሂደት እያለፉ ይገኛሉ። ፕሮግራሙ የምዝገባ ባለሙያዎች በተለያዩ ቦታዎች የምዝገባ ማዕከላትን በማመቻቸት ምዝገባ ሲያከናውኑ የቆዩ ሲሆን አሁንም ይህን የምዝገባ ሥራ እያከናወኑ ይገኛሉ።[50] በጽሕፈት ቤቱ በኩል የሚደረጉ ምዝገባዎች ለተጠቃሚ አገልግሎት በሚሰጡ አካላት (ለምሳሌ ግብር አስገቢ አካላት) ሥር የማይካተቱ ነዋሪዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ሁለተኛውና አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ይሸፍናል ተብሎ የሚታሰበው አካሄድ ተጠቃሚዎችን መሠረት ያደረገ የምዝገባ ሥርዓት (use case approach) ነው። ይህ አካሄድ ተገልጋይ ያላቸው አካላት ከፕሮግራሙ ጋር በመተባበር እና ቴክኒካዊ ድጋፎችን በማግኘት ደንበኞቻቸውን በሙሉ በራሳቸው እንዲመዘገቡ የሚደረግ አካሄድ ሲሆን በስፋት ተግባራዊ ለማድረግ የሚታሰበው ይህኛውን የምዝገባ ሥርዓት ነው። በዚህ የምዝገባ አካሄድ ተገልጋዮች ያሏቸው ተቋማት (በተለይ የፋይናንስ ተቋማት) ለምሳሌ እንደ ባንክ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ገቢዎች ቢሮዎች፣ ኢትዮቴሌኮም እና መሰል የፋይናንስ ተቋማት ከማዕከል ጀምሮ እስከ ክልሎች ወረዳዎች ድረስ ያሏቸውን ደንበኞች በዚህ ሥርዓት እንዲገቡ ምዝገባ የሚያከናውኑበት አካሄድ ነው።

የመመዝገቢያ መሣሪያዎችን የመግዛት፣ የምዝገባ ባለሙያዎችን የመመደብ እና የምዝገባ ጣቢያዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት ምዝገባውን የሚያካሂዱት አካላት ሲሆን፣ ለምዝገባ ባለሙያዎች ሥልጠና የመስጠት፣ የምዝገባ ዕቃዎቹ ሲገዙ ድጋፍ ማድረግ እና መሰል ቴክኒካዊ እርዳታ መስጠት ደግሞ የፕሮግራሙ ኃላፊነት ነው። እነዚህ አካላት ምዝገባውን አካሂደው መረጃውን ወደ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ይልካሉ፤ መረጃው

---

[49] Project Implementation Strategy, NIDP/EY/ P.21.

[50] ፕሮግራሙ የምዝገባ መሣሪያዎች እና የምዝገባ ባለሙያዎችን በማዘጋጀት በተለያዩ ቦታዎች ምዝገባ እያደረገ ይገኛል። ምዝገባውን የሚያካሂደው በአብዛኛው ሰዎች በሚበዙበት አካባቢ ሲሆን ለምሳሌ ይህ ሰነድ በሚዘጋጅበት ወቅት ምዝገባ በሳይንስ ሙዚየም፣ በፖስታ ቤት፣ በቤተ መንግሥት ፓርኪንግ ፣ በተለያዩ ክልሎች የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን፣ በቦሌ አየር መንገድ ፍልሰተኞች ወደ ሀገራቸው ሲገቡ እና በዋናው መሥሪያ ቤት እያካሄደ ይገኛል። ከዚያ በፊትም በሚሊኒየም አዳራሽ እና ሌሎች ቦታዎች ምዝገባ አካሂዷል።

በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ፕሮሰስ ተደርጎ የዲጂታል መታወቂያ ወይም ፋይዳ ቁጥር ወዲያው እንዲመነጭ ይደረጋል፡፡

በተጠቃሚዎች በኩል የሚደረግ ምዝገባ እንደሀገር ውጤታማ የሚያደርግ የምዝገባ ሥርዓት በመሆኑ በሰፊው ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ለምሳሌ በገቢዎች ሚኒስቴር ሥር የሚገኙ የግብር መለያ ቁጥር ያላቸውን ግብር ከፋዮች በመመዝገብ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ለማስገባት ፕሮግራሙ እና ገቢዎች ሚኒስቴር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመው ሥራ ተጀምሯል፡፡ ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮም ጋር በተመሳሳይ መልኩ የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሞ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በዚህ አካሄድ መሠረት ሁሉም ተጠቃሚ አካላት ደንበኞቻቸውን ወደ ፋይዳ ወይም ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት የሚያስገቡ ከሆነ፣ ከነዚህ ውጭ ያለውን የሕብረተሰባችን አካል የመመዝገብ ሥራ በጽሕፈት ቤቱ በኩል ይከናወናል ማለት ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ 8 የሚደርሱ ባንኮች ደንበኞቻቸውን መመዝገብ የጀመሩ ሲሆን፣ ሌሎች ቀሪ ባንኮች ደግሞ ወደ ምዝገባ ለመግባት የመመዝገቢያ መሥሪያዎች ግዢ እና ሌሎች ዝግጅቶችን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን መሠረት ያደረገ ምዝገባ ማለት በሀገሪቱ ያሉ የተለያዩ መዋቅሮችን በመጠቀም ምዝገባ ማካሄድ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ጤና ሚኒስቴር የጤና መድን እና ሌሎች የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቢመዘገብ፣ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ከመንጃ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ምዝገባ ቢያካሂድ፣ ግብርና ሚኒስቴር የምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ አቅርቦት ተጠቃሚዎችን ወደ ፋይዳ ሥርዓት ቢያስገባ የምዝገባ ሥራው በታቀደለት ጊዜ ማጠናቀቅ የሚቻል ይሆናል፡፡ ተጠቃሚዎችን መሠረት ያደረገ ምዝገባ፣ ምዝገባው የሚካሄደው ለተጠቃሚዎች አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት  በኩል ቢሆንም ፋይዳ ቁጥሩ ወይም ልዩ ቁጥሩ ወይም ዲጂታል መታወቂያው የሚመነጨው ከፕሮግራሙ ዳታ ሴንተር ብቻ ነው፡፡ የእነዚህ አካላት ኃላፊነት ከመዘገቡ በኂላ የመዘገቡትን መረጃ ወደ ማዕከላዊ ዳታ ሴንተር  መላክ ነው፡፡

የተመዝጋቢዎች መረጃ ወደ ዳታ ሴንተር ከደረሰ በኂላ ሥርዓቱ ባለ 12 ዲጂት ልዩ ቁጥር በማመንጨት ለተመዝጋቢዎች ይልካል፡፡ አገልግሎት ሰጪዎችም ሥርዓቱ ያመነጨውን የደንበኞቻቸውን ልዩ ቁጥር መሠረት በማድረግ የደንበኞቻቸውን ምዝገባ በአዲስ መልኩ በድጋሚ ያካሂዳሉ፡፡ አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች ከመሠረታዊ መታወቂያዎች የመነጩ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ይሰጣሉ ሲባል በዚህ መልኩ ይሆናል ማለት ነው፣ ምክንያቱም የባንክ ደብተር፣ የግብር መለያ መታወቂያ እና የመሳሰሉት አገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው፣ አንደኛውንና ሁለተኛውን የምዝገባ አካሄዶች ተግባራዊ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ ሦስተኛውን የምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ግን የፖሊሲ አቅጣጫ ማሰጠት እና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ አንደኛውንና ሁለተኛውን የምዝገባ ሥርዓት  ጎን ለጎን ተግባራዊ ማድረጉ አጠቃላይ የምዝገባ ሥራውን ውጤታማ በሆነ መንገድ በተወሰነ ጊዜ ለማጠናቀቅ የሚያግዝ ነው፡፡ ነገር ግን፣ ሦስተኛው የምዝገባ ሥርዓት ከተቋሙ ፈቃድ በመውሰድ እና ከተመዝጋቢዎች አነስተኛ ክፍያዎችን በማስከፈል የሚደረግ የምዝገባ ሥርዓት እንደመሆኑ ትርፍ ለማግኘት የሚከናወን ነው፡፡ ይህ የምዝገባ ሥርዓት የፖሊሲ አቅጣጫ የሚፈልግ በመሆኑ እና የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት የሚጠይቅ በመሆኑ በቅርብ ጊዜ ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

## 7. ማጠቃለያ

*አሁን በሥራ ላይ ያለውና እንደመሠረታዊ የመታወቂያ ሥርዓት የሚቆጠረው የኢትዮጵያ የመታወቂያ ሥርዓት የቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ሲሆን፣ ይህ የመታወቂያ ሥርዓት እጅግ ኋላ ቀር አና በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ በመሆኑ በተለይ በገጠሩ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ የዲጂታል መታወቂያ የሚያስገኛቸውን ጠቃሜታዎች እንዳያገኝ ያደረገ ነው። በቀበሌ መታወቂያ ሥርዓት ማንም ሰው ከተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ መታወቂያዎችን እንዳያወጣ ለመከላከል የሚስችል ሥርዓት የሌለው ሲሆን፣ በመታወቂያ ካርዱ ላይ ያሉ መረጃዎችም በቀላሉ ሊጭበረበሩ እና ሊቀየሩ የሚችሉ ናቸው።*

*ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉን አቀፍ፣ ወጥና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የሀገሪቱ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበትን ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት እና የተመዝጋቢዎችን መረጃ በመያዝ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። አሁን የተጀመረው የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም የነዋሪዎችን የመታወቅ መብት መንግሥት የሚያከብርበትን እና ነዋሪዎችም የመታወቅ መብታቸው በቀላሉ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ለመፍጠር ያስችላል። ይህም በአገልግሎት ሰጪዎች እና በአገልግሎት ጠያቂዎች መካከል ከፍተኛ መተማመን እንዲኖር እንደሚያደርግ የሀገራት ልምዶች ያሳያሉ።*

*አተገባበርን በተመለከተ በሕግ የተደገፈ የአተገባር ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ አዋጅ ፀድቆ ሥራ ላይ ውሏል። ሕጉ ከሌሎች ሀገራች ተመሳሳይ ሕጎች አንፃር ዘግየት ብሎ ወጣ በመሆኑ በሌሎች ሀገራት የተከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያመች አግባብ የተዘጋጀ ነው። የምዝገባ ሥርዓቱን በተመለከተም በፕሮግራሙ በኩል፣ ሌሎች የዲጂታል መታወቂያን የሚጠቀሙ ተቋማት ደንበኞቻቸውን እንዲመዘግቡ በማድረግ እና በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች በኩል እንዲከናወን በማድረግ በአጭር ጊዜ የዲጂታል መታወቂያን ለሁሉም ነዋሪ ለማዳረስ ፕሮግራሙ እየሠራ ይገኛል።* ■

## የዐበይት ሕጎች፣ ሪፖርቶችና ሰነዶች ዝርዝር


የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት

በባንኮች ላይ የሚፈጸሙ የማጭበርበር ወንጀሎች መንስኤዎቻቸውና የአፈፃጸም ዘዴዎቻቸው፣ ፍትሕ ሚኒስቴር 2014፣

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 1284/2015

Abraham, Ronald et al., State of Aadhaar report, 2017–18, ID insight, May 2018.

Digital Identification, A key to inclusive Growth, McKinsey Global Institute, 2019

ID4D 2022 Annual Report, available at https://documents1.worldbank.org/

World Bank, ID4D, Practitioners Guide, 2019,

Identification Systems for Social Protection, Center for Social Development, 2016,

Identification for Development, available at https://id4d.worldbank.org/guide/types-id-systems,

ID4D Country Diagnostic, Ethiopia, 2017,

Towards the evaluation of socio-Digital Ecosystem in Africa, Comparative analysis of findings from ten countries, Center for internet and society and research ICT Africa, 2021.

Project Implementation Strategy, NIDP/EY/